**ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ**

**Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity**

Efdpu@aol.com www.Finote.org

***የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ***
***ግንቦት 23 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ***

# ነፃነትን በሞግዚት ዴሞክራሲን በመክሊት

ለረዥም ጊዜ፤ ወያኔ፤ የቀልድ ምርጫ ለማድረግ የሚያስችለውን መስናዶ ካደረገ በኋላ፤ ብቻውን ሮጦ ራሱን በመቅደም አቸንፌአልሁ ብሎ በዚህ ሳምንት አውጇል ። ይህንን እንደሚያድርግ ደግሞ ያልተጠበቀ አልነበረም ። ደጋፊዎቹና አሽቃባጮቹም አጨብጭበውለታል ። የበላይ ጠባቂዎቹና ዐለቆቹም "አባጀህ ልጃችን ! "ብለውታል ። የአገልጋይነት ዘመኑን እንዲራዘምላቸው መረጋገጫ ስለገኙም፤ በደስታ ፈንድቀዋል ። ኢትዮጵያና ዜጎቿ ፤ ወደ ሌላ የመከራ አጋዛዝ መሽጋገራቸውን ግን አልተረዱትም። ሊረዱትም አይችሉም። ቀድሞውንም ቢሆን፤ ጉዳያቸው አልነበረምና !

ይህንን ሳይታለም የተፈታውን የምርጫ ዝባዝንኬ ለማሳወቅ፤ አስቀድመው የወሸከቱ የባዕድ ሀገሮች ባለሥልጣናትም፤ ምርጫው ዴሞክራሲያዊና ፍትኃዊ ነበር ለማለት እንደሚሽቀዳደሙ አስቀድመን አውቀናል። ቀደም ብለውም ያልጠየቋቸውን ዘበራርቀዋልና! እኛን ግን ውትሮውንም ቢሆን፤ አላሰገረምንም ። ምክንያቱም፤ የምዕራባውያኑ ወያኔን ዐይን ባወጣ መልኩ መደገፍ፤ ከጥቅማቸው ጋር የተቆራኘ በመሆኑ፤ ጥቅማቸውን የሚጠብቅላቸውን ታማኝ አገልጋይ መርዳት የዱብ-ዕዳ ከስተት አልነበረም ።

በጥቅም ውስብስብ የታወረው የዓለም ዲፕሎማሲ ፤ ለሰው ልጅ መብት፤ ነፃነትና ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ፤ደንታ ስለማይሰጥ፤ ምዕራባውያኑ፤ በወያኔ መሪዎች ላይ ተፅዕኖ አሳድረው ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጩኸት የሳማሉ ተብለው አይጠበቁም ። ብልሃቱን መፈለግ ያለብን እኛው ራሳችን ብቻ ነን ። የእስከዛሬው የሕዝብ ጩኸት ፤ ሰሚ ጆሮ አላገኘም ። በመሆኑም፤ እንደ ገደል ማሚቶ ( ኤኮ) የተቆጠረብንን ሰሚ ያጣ ባዶ ጮኸታችንን ወደ ተግባር ለውጠን ውጤት አስመዝጋቢ ተግባር ካላከናወንን፤ የዘረኛው አገዛዝ መሳቂያ መሳለቂያ ሆነን እንቀራለን ። ይህ አስነዋሪ ታሪክ ደግሞ ፤ ለትውልድ የሚያስተላልፉት አሳፋሪ ውርስ ሆኖ ይቀራል ።

ይህንን የፌዝ ምርጫ፤ አስቀድመው በሰፊው ገምግመው፤ ምንነቱን በዝርዝር ያስረዱ ብዙ ምሁራንና የሕግ ባላሞያዎች ነበሩ። ይህም፤ ኢትዮጵያውያንንና የውጭ ታዛቢ ምሁራንን ያጠቃልላል፡፡ ሁሉም፤ ምርጫው ዋጋ ቢስ እንደሚሆንም ተንትነው ጽፈዋል ። የኢትዮጵያ ሕዝብም፤ ምርጫውን እንደ ተበላ ዕቁብ ቆጥሮ ዋጋ አልሰጠውም ። ዋጋ ቢስ በሆነው የወያኔ ምርጫ ጊዜንና ጉልበትን ማጥፋት ፤ " በፈርስ ላይ መጓጎር" እንደሆነ ቆጥሮታል። ለድል ወደሚያበቃው ትግል ከመሸጋጋር በቀር፤ ሌላ አማራጭ እንደማይኖረው ተረድቶ ተዘጋጅቷል ።

ሕዝቡ፤ ይህንን ምርጫ ፤ ልክ " በየዓመቱ የበልግ ወራት፤ አሮጌ ቆዳውን ሸልቅቆ በሌላ መርዘኛ ቆዳ እንደሚተካው የዕባብ ገላ " አድርጎ ፈርጆታል ። የዕባብን መርዝ ከማጥፋት በቀር፤ ሌላ ብልሃት

እንዳማይኖርም ተረድቶታል ። ወደ ሚቅጥለው የትግል ምዕራፍ ከመሸጋገር በቀር፤ ላለፈው ክረምት ቤት ለመስራት የሚሞክር ማንም ኢትዮጵያዊ የለም። ኢትዮጵያ፤ የብልሃተኞች ሀገር መሆን ካለባት፤ አዲስ ብልሃት በመፍጠር፤ የተሻለ ሥርዓት ለማምጣት ትግሉን አጠናክሮ ከመቀጠል በቀር፤ ከዚህ ምርጫ በኋላ፤ ስለሚፈጠረው ሁኔታ ፤ እንዲያው ማሰላሰል ፤ ትርፉ ከንቱ ድካም ነው ።

ዴሞክራሲያዊ መብቶች በታፈኑባት ሀገር፤ በአንድ ብሄር የበላይነት የተዋቀረ ብቸኛ ፓርቲ ሥልጣን በያዘበት ሁኔታ፤የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎችና ጋዜጠኞች ወኅኒ ቤት እየማቀቁ እያሉ ፤ ነፃና ፍትኅ የሰፈነበት ምርጫ ተካሄዷል ማለት፤ ቢያንስ የኢትዮጵያን ሕዝብ የማሰብ ችሎታና ለዕልና መሳደብ ይሆናል ። በዓለም አቀፍ የምርጫ መሠረታዊ መስፈርት ላይም ማፌዝም ጭምር ነው ።

" ሲፈጭ የነበረ፤ ሲነፋ ከበረ " እንደሚባለው ብሂል፤ ከትላንት በስቲያ በፊውዳል ሥርዓት ሲበደል ለነበረና፤ ትላንትም፤ በወታደር አምባገንን አገዛዝ ሲማቅቅ ለቆየው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ይህ ምርጫም ይበዛባታል ካልተባለ በስተቀር፤ የወያኔ ምርጫ፤ ዲሞክራሲያዊም ፍትሃዊም፤ አይደለም። በዚህ ከንቱ እምነት ሊያምኑ የሚፈልጉ ካሉ ራስን የመደለል በሽታ ሰለባ የሆኖ መሆን አለባቸው። እራሳችውን እየደለሉ፤ የውርደት ህይወት ለመኖር የሚሹ ካሉ፤ እየሞቱ የሚኖሩ መሆናቸው ሊረዱት ይገባል ። እየሞቱ መኖር ግን ህይወት የሌለው ኑሮ እንጅ፤ ህያው የሆነ ህይወት አይደለም ።

ወያኔዎቹና አለቆቻቸው ከፈለጉ፤ እራሳቸውን ሊያታልሉ ይችላሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብም ግን፤ ራሱን የማታለል ባኅል የለውም። የባዕዳንን ቅኝ ግዛት ተቋቁሞ ነፃነቱን ጠብቆ የኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ፤ ለአምስት መቶ( 500 ) ዓመታት በእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ሲምቅቅ የኖረው የህንድ ሕዝብ እንኳ፤ በዓለም ደረጃ፤ አስተማማኝ የዴሞክራሲ ሥርዓት ሰፍኖባታል በምትባለው ሀገር የዴሞክራሲ መብቶችንና ነፃነትን ተጎናጽፎ ይኖራል ።

ታዲያ እኛ ምን ጎድሎብን ነው የወያኔ ምርጫ ይበቃችኋል የምንባለው ? ደግሞስ ከመቸ ወዲህ ነው፤ እንደ ለማኝ ቆሎ ፤ ለአንድ ሕዝብ ፤ ዴሞክራሲ በቆለምሽሽ ይበቀዋል ተብሎ የታወጀው ? ሰፊውን ሌማት ማን ወስዶበት ? ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ነፃነትና ልዕልና፤ ደሞክራሲያዊ አስተዳደርና የልማት ዕድገት ወሳኙ ማን ነው? ይህንንና ተዛማች ጥያቄዎችን እየጠየቀ መልስ ማግኘት ያለበት ራሱ ባለቤቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ። ማንም አልፎ -ሂያጅ፤ ሊሰጠውም ይሁን ሊነፍገው አይችልም ። ይህንን ጥያቄ እየጠየቀ፤ የራሱን መልስ አግኝቶ ነፃነቱንና ሀገራዊ ልዕልናውን ካላስከበረ፤ ዘለዓለም የደም ዕምባ እያነባ እንደሚኖር ያውቀዋል ። ቢሆንም፤ የፈለገው ዓይነትና ክብደት ያለው መከራና ስቃይ ቢፈራረቅበትም፤ ነጻነትን በሞግዚት፤ ዴሞክራሲን በመክሊት፤ እንዲቸርለት የሚፈልግ ሕዝብ እንዳልሆነ አኩሪ ታሪኩ ይመስክርለታል።

ላለፉት 24 ዓመታት የቀልድ ምርጫዎች በወያኔ የቲያትር መድረኮች ተፈራርቀዋል። በዚህ ሂደት፤ አንድ የአምባገነን ዘረኛ ፓርቲ ብቻውን እንደ ሽምብራ ቂጣ እየተገለባበጠ ሥልጣኑን ሲያረጋግጥበት ቆይቷል። የዴሞክራሲ ጭንብል፤ በቅብዐ ሜሮን ጠበል ከባዕዳኑ አለቆቹ ተረጭቶለታል። ይህም ሊሆን የቻለበት ዋናው ምክንያት፤ ሀገራችን በታሪኳ፤ እንደ ወያኔ የኢትዮጵያን ሀገራዊ ጥቅምና ክብር ለባዕዳና አሳልፎ የሰጠ መንግሥት ስላልነበረ ነው ። ባለቤት ያጣ ሀገር ፤ በሩ ክፍት፤ የጓዳው ምሥጢር ፤

ዝርክርክ ይሆንና፤ የአልፎ-ሃጂዎች መጫዎቻ ሆኖ ይቀራል ። የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ላይ ትገኛለች። ሀገሪቱ፤ በታሪኳ፤የባዕዳኑን ወረራዎች ሁሉ ተከላክላ ነፃነቷን ጠብቃ ልትኖር ካስቻሏት ዐበይት ምክንያቶች መካከል፤ ዜጎቿ የሀገራቸውን ሁለንተናዊ ምሥጢር ተባቂዎች መሆናቸው ነበር። " **ምሥጢርህን በጉያ፤ ስንቅህን በአህያ** " የሚለው ይትበሃል፤ በሁሉም ዜጋ ልብ ተቀርፆ ይኖር ነበር። ዛሬ ይህ ዕምነትና አሰራር ምን ያህል ክብደት እንደሚሰጠው ማወቅ አይቻልም።

አዲስ አበባ ዛሬ፤ የዓለም አቀፍ ከተማ መሆኗ፤ የሰላዮች መናኻርያና መራኮቻ አድርጓታል። ወሬና መረጃ አቅራቢዎች ይተረማመሱባታል። ከቁጥጥር ውጭ የሆነው ድኅነቱም፤ እኳንስ ሀገርን ቀርቶ፤ እናትንና የራስንም ሰብዕናም ቢሆን ለመሸጥ ያስገድዳል። ምናልባት፤ በቅደም- ተከተል፤ ማስቀመጥ እሚቻል ከሆነ፤ የሰው ልጅ መሠረታዊ ጥላቶቹ፤ አራት እንደሆኑ ብዙዎቹ ይስማሙበታል።

እነርሱም፤ 1ኛ. ድንቁርና ( አለማወቅ) 2ኛ. ባርነት ( ነፃነት ማጣት) 3ኛ. ድኅነት 4ኛ. በሽታ ሳይሆኑ አይቀሩም ተብሎ ይታመናል ። እነኝህ አራት የሰው ልጅ ጠላቶች፤ በሀገራችን ስር ሰደውና ተንሰራፈተው ይገኛሉ። የሕዝባችን ቀንዳኛ ጠላቶች የሆኑትን እነኝህን ደመኛ ባላንጣዎች ሁላችንም ተባብረን ካላስወገድናቸው፤ ዝንት-ዓላማችንን ከእነርሱ መዳፍ ልንወጣ አንችልም ። ከእነርሱ ለመላቀቅ ደግሞ፤የማሰብና የመንቀስቀስ ነፃነት ችሎታችንን አፍኖ የያዘውን ዘረኛ ሥርዓት መስወገድ የመጀመሪያው ተግባራችን አድርገን መነሳት ይኖርብናል ። በየአምስት ዓመታቱ በቀልድ መርጫ እያፌዘ ዕድሜውን እንዲያራዝም ልንፈቅድለት አይጋባም ። በቃ ማለት፤ ትርጉሙ በቃ ነው። በቃ ብለን ጨክነን ካልተነሳን፤ ተዋርደን መቅረታችን ልንዘነጋው አይገባንም ።

ነጻነትን ለሚያስገኝ ትግል ፤ የጊዜ ቀጠሮ ልንሰጠው አይገባንም። የችግራችንን ፍጻሜ ወደ ነገ ካስተላለፍነው አይወገድም ። የነቀል- ተከል ፖለቲካ፤ የእርስ በዕርስ መናናቅና መጠላለፍ ፤ የውቂ-ደብልቂው ውይይትና ንትርክ ፤ እስካሁን የትም አላደረሰንም። ድርና ማጉ በጠፋበት የትግል አቅጣጫ መንከራተት ውጤትን አላስመዘገበልን ።

እስከ ዛሬ ደረስ የተጓዝንባቸው መንገዶችና የተደረጉት ጥረቶች ሁሉ የትም እንዳላደረሱን አውቀውብን ፤ የኢትዮጵያ ጠላቶች፤ ንቀውናል ። የትም አይደርሱም ብለው አፌዘውብናል ። " ውሾቹም ይጮኻሉ፤ ግመሎቹ ግን የራመዳሉ ! " ብለው ተዘባብተውብናል ። " ጦርነትን መዋጋት ብቻ ሳይሆን፤ ጦርነትን የመፍጠር ችሎታ አለን " እያሉ ተመጻድቀውብናል ። የትም አይደርሱ ተብለው የተናቁትን ያህል፤ " የናቁት ፈረስ ጠለ በደደስ " የተባለውን ይትብሃል በተግባር ለመትርጎም ችለዋል። ይህ ሁሉ ሊቆጨን በተገባ ነበር ። ግን እስካሁን አልሆነም።

የወያኔዎቹን የቀልድ ምርጫ ፤ ለእነርሱ ዳንኪራ መርገጫ እንተወውና፤ ስንት አማራጮች አንግበው እንደሚጓዙ ማስተዋል አግባብነት አለው። በእነርሱ በኩል፤ ከመነሻቸው ጀምሮ ፤ሦስት አማራጭችን ይዘው ይንቀሳቀሳሉ።

1ኛ. ሥልጣኑን ጨብጠው እስከቀጠሉ ድረስ ኢትዮጵያን እንደ ሰም አቅልጠው እንደ ገል ቀጥቅጠው እያገዙ ሀብቷን መበዝበዝ የቅድሚያ አጀንዳቸው መርጫ ነው። ይህንን የመጀመሪያ መርጫቸውን

ባስተማማኝ ሁኔታ ለመከናወን፤ የዘረኛ አገዛዛቸውን በሁሉም ረድፍ የተጠናከር ኃያል/ ሥልጣን ያለው "መንግሥት " (ቶታሊታርያን አገዛዝ ) መቋቋም ነበር። ይህንንም ማደረግ ተሳክቶላቸዋል። ከመቶ አምሳ እጅ 50% የሆነውን የሀገሪቱን ሀብት ተቆጣጥረዋል ። ምናልባትም በአፍሪካ ቀንድ ትወዳዳሪ የለውም የሚባለለትንም የጦር ኃይል አደራጅተዋል። በአንድ ብቸኛ ብሄር የተዋቀረ አምባገነን የገዥ ፓርቲ ለ 24+ ዓመታት በሥልጣን እንዲቆይ ተደርጓል። የወያኔ የዕለት-ዕለት ጭንቀት፤ የኅለውና ( የሞት-ሽረት ) ጥያቄ በመሆኑ፤ ኅልውናውን ለመጠበቅ የሚያስችለውን፤ ሁሉ አቀፍ የስለላ ድረጅት መስርቷል ። በዚህ የስለላ ድርጅት አማካኝነት፤ ተቃዋሚዎቹን ሁሉ ለመቆጣጠር፤ ለማሰርና ለማጥፋት አስችሎታል ። ሕዝብን አፍኖ ፤ ጸጥ -ለጥ አድርጎ ለመግዛትም በቅቷል ። ይህንን ለማደረግ የሚይስችለውንም ማነኛውንም የመጨቆኛ መሳሪያዎችንና ታቋማትን ይጠቀማል። ይህ አገዛዝ፤ በሥልጣኑ መቆየት እስከቻለ ደረስ ፤ሀብት እያበዘበዘ ዕድሜውን አራዝሞ ይቀጥላል ። ይህ የመጀመሪያ አምራጩው ነው።

2ኛ. የኢትዮጵያ ሕዝብ አልጋዛም ባይነቱን ወደ አሻፈረኝነት ለውጦ አመፁ እየተጋጋለ መሄዱን ሲረዳ፤ የህልውናው ሁኔታ አደገኛ ደረጃ መድረሱን ሲያውቀው ፤ ወያኔ ወደ ሁለተኛ ምርጫው ለመሄድ ይገደዳል ። ሁለተኛ መርጫው ፤ ትግራይን አስገንጥሎ ነፃ የትግራይ ሪፑብሊክ መመስረት ይሆናል ። ይህንንስ አያደርግም የሚሉ ተላላዎችና ዝንጉዎች እንደሚኖሩ አንስተውም ። " ከኢትዮጵያ የወርቅ ማዕደን ላይ የተቀመጠ ቡድን፤ እንዴት አድርጎ መገንጠልን ይፈልጋል ? " ብለው የሚጠይቁ ካሉ፤ "ኤርትራውያንስ ትላንት በኢትዮጵያ የወርቅ ማዕድን ላይ ተቀምጠው አልነበረም እንዴ ? " የሚለውን ጥያቄ እንዲመልሱ ይጠበቅባቸዋል ።የአሁኗ ኢትዮጵያ በዕርግጥ የወያኔ ጥቅም የምታስጠብቅ ሀገር ሆናለች። ጥቅማቸውን እስከጠበቅችላቸው ድረስ ደግሞ፤ ሊቆዩባት ይችላሉ። ነገር ግን፤ " የትግራይን ጥቅም የማታስጠብቅ ኢትዮጵያ፤ ጥበጣጠስ " ብለው የመጡ ሰዎች በመሆናቸው ፤ ጥቅሚን በብቸኝነት መጠቅም ከማይችሉበት ደርጃ መድረሳቸውን ሲያውቁ፤ " ዳህን ኹኒ አቲ አዲ ፤ ካብ ቕድሚ መፍረስኺ " ደህና ሁኚ አንች ሀገር ከመፍረስሽ በፊት " ብለው ጠንጥነዋት እንደሚሄዱ፤ እነርሱም አይክዱትም ። ለመገንጠል የሚያበቃቸውን ቅድመ-ዝግጅት ሁሉ አጠናቅቀው ጨርስዋል ። የሚከተሉትን ሀቆች መገንዝብ ይጠቅማል።

ሀ) ከወሎ፤ ከጎንደርና ከአፋር ስፊና ለም መሬቶችን ወደ ትግራይ አጠቃልለው አስገብተዋል። ትላንት ከነበራት የቅዳ ስፋት፤ ዛሬ የትግራይ ጥቅላይ ግዛት በሦስት እጅ አድጋለች። ይህም ነገ ለምትመሠረተው አዲስ ነፃ ሪፑብሊክ ሰፊ የኢኮኖሚ መሠረት እንዲሆን ታስቦ ነው። በጎንደርና በወሎ ኢትዮጵያዊ ሕዝብ ኪሳራ፤ ትግራይን ገንብቶ ነፃ ሀገር የማድረግ ኅልምን ዕውን ለማደረግ ! ዛሬ ዐይኑ እያየ፤ ዦሮው እየሰማ " እነርሱ ምን ያርጉ ፤ ከኛ ሰው ሲታጣ " እያለ ያጉረምርማል፤ የወሎና የጎንደር ሕዝብ!

ለ) ላለፉት 24 ዓመታት፤ ትግራይን ሁሉ-አቅፍ በሆነ መሥሰረት ልማት ገንብታዋታል። ታላላቅ የልማት፤ ባንኮችና የንግድ የትምህርት ተቋማት ተድራጅተው ተመስርተዋል። ፋብሪካና እንዱስትሪዎች ይንቀሳቀሱባታል ። የተማረና፤ በልዩ ልዩ ሙያ የሰለጠነ የሰው ኃይል ተከማችተዋል። ይህ ሁሉ የሚደረገው ያላግባብና ህገ-ወጥ በሆነ ማንገድ ከሚዘረፈው በኢትዮጵያ ሕዝብ አንጡራ ሃብት በመሆኑ እንጅ፤ ትግራይ ለምን ለማች ብሎ ዐይኑ ደም የሚለብስ ኢትዮጵያዊ የለም ።

ሐ) ነገ የሚገነጥሏትን ትግራይ፤ የዓለም አቀፍ ወሰን እንዲኖራት ታስቦ፤  ከሱዳን ጋር የሚያዋስነውን የኢትዮጵያን ምዕራባዊ ግዛት በማጠቃለል፤ ከሱዳኖች ጋር የቅድሚያ ስምምነት አድርገዋል። የሱዳንን ዕውቅናም አግኝተዋል ። የባኅር ወደብ ጥቅም ለማግኘት የሚያስችላቸውንም ቅድመ ዝግጅት ከጂቡቲና ከሱዳን ( ፖርት ሱዳን ) ዋስትና አግኝተዋል ። ከከሰላ -- መቀሌና እንዲሁም፤ ከጅቡቲ --- መቀሌ የሚያገናኙ  የየብስ መንገዶች ታዘርግተዋል ወይም እየተዘርጉ ናቸው። አስብና--- ምፅዋንም ከመጠቅም የሚከለክላቸው አይኖርም።

መ) የጠነከረ የትግራይ መከላካያ ጦር ግንብተዋል ። የኢትዮጵያን የምድር፤ የአየርና የኮማንዶ ጦር ወደ ትግራይ አዛውረው፤ በአንድ  ማዕከላዊ ዕዝና ቁጥትር ስር አድርገውታል ። የኢትዮጵያ አየር ኃይል ጠቅላይ ሰፈር/ መምሪያም መቀሌ ውስጥ  ነው። ማነኛውም ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ትግራይ ውስጥ እንዲከማች ተደርጓል ። ይህ ሁሉ ጥረት፤ ነገ ነፃ  የትራይን ሪፑብሊክ ሲያውጁ ለአዲሲቱ ሀገራቸው በቂ የመተማመኛ መከላካያ ሠራዊት አዝጋጅቶ ለመጠበቅ ነው።

ይህንን ሁሉ ሥራ ካከናወኑ  በኋላ፤ ትግራይን አስግንጥሎ ለመውሰድ ይሳካላቸዋል ብለን አናምንም። ምክንያቱም የትግራይ ሕዝብ ለዚህ  እኩይ ተግባር የተባበራል ተብሎ ስለማይጠረጠር ነው። የትግራይ ሕዝብ፤ የኢትዮጵያዊነት ብኩርናውን ፤ በጭብጥ ምስር የማይለውጥ መሆኑን ከማንም በላይ እኛ በቅርብ ያየነውና የምናውቀው በመሆኑ፤ ወያኔ፤ ሦስተኛው አማራጩ አይሳካለትም ። ይህ አለመሳካቱን ሲረዳ፤ ወደ አራተኛውና የመጨረሻው አማራጭ ለመሄድ ይገደዳል ።

3ኛ አማራጩ ደግሞ፤ የመጨረሻ አጥፍቶ የመጥፋት የክኅደት ርምጃው ይሆናል። ሁሉንም አማራጮች ሞክሩ ካላዋጣው፤ የመሸሸ እቅዱን አዝጋጅቶ ተቀምጧልና እስከዛሬ በየቦታው የቀበረውን ጊዜውን እየጠበቀ የሚፈንዳውን ቦምብ አቅጣጥሎ ፤ሲጠላት የነበረውን ሀገር፤ የመጨረሻ ግብዐተ- መሬቷን ማየቱን ይመኛል ። " የአንድ መቶ ( 100 ) ዓመት ብቻ ታሪክ ያላትን ሀገር፤ አንድ መቶ ዓመት ባልሞላ ጊዜ  እንዳልነበረች እናደርጋታለን  " ባሉት መሠረት፤ ወያኔዎቹ መኞታቸውን እውን ለማደረግ ይመኛሉ። ይህ ግን ፤ እኛ ከንዳችንን ሳንተራስ  አይፈፀምም ! የሚሆነው ተቃራኒው ነው ።

በመጨረሻው ሰዓት፤ ሮም ስትቃጠል፤ ደስታ እንደተሰማው የሮማ ንጉሥ ኔሮ ሁሉ፤ ወያኔም ኢትዮጵያን ስትቃጠል ማየት የተለይ ደስታ እንዳሚሰማው እናውቃለን  ። ይህ ግን ፈፅሞ አይሆንም። የሚሆነው፤ በጠላቶቿ ከርሰ-መቃብር፤ የኢትዮጵያ ትንሣዔ መታወጅ ይሆናል ።

ባሁኑ ወቅት ወያኔ አራት አማራጮችን ይዞ ሲንቀሳቀስ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ሁሉት  አማራጮችን ብቻ ይዞ ተቅምጧል ። እነኛህ ሁለት አማራጮች

ሀ) አምፆ በመነሳት፤ ይህንን አጥፊ ዘረኛ አገዛዝ ማስወግድ ፤

ለ ) እየተገዙ በባርነት ውስጥ መኖር ናቸው።

ምንም ተባለ ምንም፤ ነፃነትን ፤ በሞግዚት ፤ ዴሞክራሲን በመክሊት ሊሰጥ የሚደፍር ማንም ኃይል የለም ። ይህንን ድፍረት ለማስማትና ለማቀበል የተዘጋጅን ሕዝቦች አይደለንም ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም መኖሯን ትቀጥላለች